

Source፡ (http://www.goolgule.com/)

# እንባየም ደረቀ!

ዘመን ተለዋውጦ፣
ተራራው ተንዶ፣
ሸለቆው ተደፍኖ፣
ልጆች ተሯርጠው የተሸሸጉበት፣
ማን ይቀደም፣ ማን ይቅደም፣
እየተጫወቱም
እልል አገኘሁህ ከተደበቅህበት፤
እያሉ እየጮሁ ልብሱን በመጎተት፣
የተደበቀውን ገልጠው ያገኙበት።
ዛፉም ተነቃቅሎ
ቁጥቋጦውም የለ የተጠለልንበት፤
ለማን ልናገረው አለች የኮንሶ እናት።

እንዲህም አወጀች፣
ተፈጥሮ መርቆኝ፣
ዘጠኝ ወር አርግዤ
አምጬ ና ብየው
እሽ ብሎ መጥቶ
ዋይ! ዋይ! እያልሁ ልጬህ ለሕፃኑ ልጅ
ገና ጸሐይ ሳይሞቅ በስር ቤት ማቀቀ፤
ባነባው፣ ባነባው፣ እንባየም ደረቀ።

ድሮ እንደ ለመድሁት፣ ዛሪስ ሞኘነቴ፤
ጠንክሪ ማማጤ።
ወደ ውጮች ዙራ እንዲህ ትማለለች
የኮንሶዋ እናት፣
አወይ ሕፃንነት፤
ነቁጥ የሌለው ፍጥረት።
ባነባው፣ ባነባው፣ እንባየም ደረቀ፣
በተሸፈንህበት በዚያ በማህጸኔ፤
ምንው ከዚያው ባደግህ፣
በኔ አይን እያየህ ጨካኙን ወያኔ።
ስሙም አይገባኝም የሚሉት "ሕዋህት"፣
አጎረህ በሥር ቤት፣
ገና እትብትህ ሳይደርቅ፤
እንድትለምድ ብሎ የኑሮን መማቀቅ።

እንሰሶች ፍረዱኝ
በዱር በገድሉ
መውለድ የምታውቁ፣
አጋዚ የሚሉት ሰው በላ አረመኔ
ቀጫጫውን ሕጻን፣ ገና ጸሐይ ሳይሞቅ
ከጡቴ ገንጥሎ፤
እስር ቤት አጎረን ማን አለብኝ ብሎ።
እንዲዚህ እያለ አፉን ሞልቶ ዛተብን፤
“መሪቱን ነው እንጅ ከናንተ ምን አለን።”
አረ ባአላህ ብለህ ብየ እንዳለምነው
አምልኮም አያውቅም፣ ባህልም አይገዛው፤
እንሰሶች ፍረዱኝ፣ ማነው ያሳደገው?
ዋይ! ዋይ! እያልሁ ልጩህ ለሕፃኑ ልጀ፣
ገና ጸሐይ ሳይሞቅ በስር ቤት ማቀቀ፤
ባነባው፣ ባነባው፣ እንባየም ደረቀ።

“ኮንሶ - የግፍ ምድር!” በሚለው ጽሁፍ የተመሰረተ (Ethiomedia.com/http://www.goolgule.com/)

© ለምለም ፀጋው በኮንሶ አራሷ ከጮርቃ ሕጻኗ ገር ለታሰረቸው የአቤቱታ ድምጽ